የኢፌዲሪ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት
FDRE TECHNICAL & VOCATIONAL TRAINING INSTITUTE

# የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት

## የህፃናት ማቆያ የአሰራር መመሪያ



**ጥቅምት2016ዓ.ም**

## ምስጋና

የሴት ሰራተኞች ተግዳሮቶች ናቸው ተብለው ከታቀዱት ፍሬያማ ተግባራት አንዱና ትልቁ ጾታ ተኮር የሆነ፣የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንዲሁም የህጻናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚቋቋሙ የህጻናት የቀን ማቆያና መንከባከቢያ ማዕከላት አገልግሎት (child day care center service) ተጠቃሽ ነው፡፡ሴት **“የመንግስት ሠራተኞች ህጻናት ልጆቻቸውን የሚያጠቡበትና ህጻናቱን የሚንከባከቡበት የህጻናት ማቆያ ማቋቋም እንዳለበት በማመን ለ**ኢንስቲትዩቱ ይህንን የሕፃናት ማቆያ ፣ የስፖርት መዝናኛ ፣የመጀመሪያ ሕክምና መስጫ ለማቋቋም የሚያስችሉ ግብዓቶችን ድጋፍ ላደረጉልን«የኢትዮ-ጀርመን /KFW/ ትብብር በማድረጋቸው ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

## መግቢያ

በየፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀፅ 48(2) መሠረት የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የህፃናት እንክብካቤ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

በመሆኑም የኢንስቲትዩቱ ሴት ሰራተኞችከወሊድ በኋላ ወደ ስራ ገበታቸው ሲመለሱበሚሰሩበት ተቋም ውስጥ ህፃን ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉና እየተንከባከቡ ለመስራት የሚችሉበትን የተመቻቸ የስራ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሴት ሰራተኞችበመውለዳቸው ምክንያት በተመደቡበት የሥራ መስክ ያለምንም ስጋትና ሃሳብ ሙሉ ኃይላቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጊዜያቸውን ተጠቅመው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል፣እንዲሁም ትውልድን የመተካት ሃላፊነታቸውን በመወጣታቸው ምክንያት የስራ ዋስትና እንዳያጡ ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 36(1) (ሐ) መሰረት ህፃናት ከወላጆቻቸው ማግኘት የሚገባቸውን ተገቢውን እንክብካቤ የማግኘት መብት እንዳላቸው የተቀመጠውን ድንጋጌ ሴት የመንግስት ሰራተኞች ሃላፊነታቸውን ለመወጣት እንዲችሉ በሚሰሩበት አካባቢ የህጻናት ማቆያ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣እንዲሁም ህጻናት የእናት ጡት ወተት በተገቢው ሁኔታ አግኝተው ለጤናቸውና ለአምሯዊ እድገታቸው የሚያስፈልጋቸው ድጋፍና እንክብካቤ አግኝተው እንዲያድጉ ለማድረግ፣

ተሻሽሎ በወጣው የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 48(6)መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሴት ሰራተኞች ህጻናት ልጆቻቸውን የሚያጠቡበት የህጻናት ማቆያዎች ሊያሟላላቸው የሚገባቸውን ዝቅተኛ መስፈርቶችና የሰው ሃይል የሚወስን መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣ ኢንስቲትዩቱም ሴት ሠራተኞች ሕፃናትን የሚንከባከቡበት የህጻናት ማቆያ ማቋቋም በማስፈለጉ በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 48(6) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርእስ**

   ይህ መመሪያ "የኢንስቲትዩቱ ሴት ሰራተኞችየህፃናት ማቆያ ማዕከል የአሰራር መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር

   2.1 "ሕጻን" ማለት የእናቱን ጡት የሚጠባና ከአራት አመት በታች ያለ ሆኖ የእናቱን የቅርብ ክትትል የሚፈልገው ሕጻን ነው፡፡

   2.2 "የሕፃናት ማቆያ ማዕከል" በኢንስቲትዩቱ ውስጥ የተቋቋመው የሕጻናት ማቆያ ማእከል ነው፡፡

3. **የመመሪያው የአፈጻጸም ወሰን**

   ይህ መመሪያ፣

   3.1 በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥረው ለሚሰሩ ሴት ሰራተኞች እና ከ4 አመት በታች ባሉ ህጻናት ነው፡፡

3.2 በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩትውስጥ በተቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎችና የህጻናት ማቆያው ውስጥ በተመደቡ ሰራተኞችላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**4. የመመሪያው አላማ**

4.1 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት ሠራተኞች ከሕፃናት ልጆቻቸው ርቀው በሚሰሩበት ተቋም ውስጥ ሙሉ ትኩረታቸውንና አቅማቸውን በተሰማሩበትና በተመደቡበት የስራ መስክ ላይ አለማድረጋቸውና ከህፃናት ልጆቻቸው ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ ከስራ ገበታቸው መቅረታቸው በራሳቸው ዕድገት፣ አቅም፣ ቅልጥፍና፣ብቃትና በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲሁም የራሳቸውን የኢኮኖሚ አቅም ከማሳደግና ራስን የመቻል እንቅስቃሴያቸው ላይ እያሳደረ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ፣

4.2 ሕጻናት እናቶቻቸው በስራ ምክንያት በአቅራቢያቸው ባለመኖራቸው ማግኘት የሚገባቸውን እንክብካቤ አለማግኘታቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በጤንነታቸው፣ በደህንነታቸው፣ በአስተሳሰባቸው፣ በቅልጥፍናቸው፣ በፈጠራ ክህሎታቸው፣ በአካላዊና አዕምሯዊ ዕድገታቸው፣ ብስለታቸው፣ በትምህርት የመቀበል አቅማቸው፣ በራስ የመተማመን መንፈሳቸው፣ ሃሳብን በነፃ የመግለፅና የማዳመጥ ክህሎታቸውና የማገናዘብ ብቃታቸው ላይ እያስከተለ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ፣

4.3 በኢንስቲትዩቱ የተሰማሩ ህፃን ልጅ ያላቸው መምህራንና ሰራተኞች በተሰማሩባቸውና በተመደቡባቸው የስራ መስኮች ላይ ሙሉ አቅማቸውን፣ ዕውቀታቸውንና የስራ ጊዜያቸውን ተጠቅመው መስራት ባለመቻላቸውና በተደጋጋሚ በልጆቻቸው ምክንያት ከስራ ገበታቸው ላይ ባለመገኘታቸው በተቋሙ በሚሰጡት የስልጠና ሂደት በተቋማቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ለመከላከል፣

**4.4** የኢንስቲትዩቱ የህፃናት ማቆያ አገልግሎት መስጫ ማዕከል በማቋቋም በተለይ በሴትሰራተኞች ላይ የሚደርሱ ጫናዎችን ለመቀነስ፣ የሴቶችን ውጤታማነት ለማሳደግና ለህፃናት በቂ እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የህጻናት ማቆያ አደረጃጀት</u>

**5 አካላዊ መዋቅር**

በኢንስቲትዩቱ የሚቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎች የሚከተሉትን አሰራሮች ተከትለው መደራጀት ይኖርባቸዋል፣

5.1 **የቦታ መረጣ/ልየታ፡-** በማዕከሉ ተጠቃሚ የሚሆኑት ህፃናት እንደመሆናቸው ማዕከሉ ሲቋቋም የቦታ መረጣው በህፃናቱ ጤናና አካል ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ኬሚካሎች፣ ብናኞች፣ ጨረሮችና ሽታ የማይደርስበት፣ የድምፅ ብክለት እንዳይኖረው ከመኪና መንገድና ድምፅ ካላቸው ወርክሾፖች የማምረቻ ቦታዎች የራቀ፣ በቂ የፀሐይ ብርሃንና አየር ያለበት ቦታ ሊሆን ይገባል፡፡

5.2 **ውስጣዊ ይዘት፡-**

- በማዕከሉ ህፃናት ጊዜያቸውን በጨዋታ የሚያሳልፉበት ክፍል ዋነኛው አስፈላጊ ክፍል ሲሆን ይዘቱም ደህንነቱ የተጠበቀና በህፃናት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች የፀዳ ሊሆን ይገባል፡፡

- ክፍሉ ለተንከባካቢዎች በማንኛውም ሰዓት በነፃነት ክትትል ሊያደርጉ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚፈጥርላቸው ሊሆን ይገባል፡፡ የክፍሉ አቀማመጥ ለህፃናት ነፃነት፣ ደህንነትና ምቾት ሊሰጣቸው የሚችል ሆኖ ሊዘጋጅና በቂ የተፈጥሮ ብርሃንና አየር ሊያገኝ በሚችል መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- በማዕከሉ የሚገኙት ክፍሎች የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡና የተለያዩ ሊሆኑ የሚገባቸው ሲሆን ለህፃናቱ እንደ ዕድሜ ደረጃቸው የመጫወቻ ክፍሎች፣ የመኝታና የማረፊያክፍሎችን፣ የምግብ ማዘጋጃና ማከማቻ ክፍል፣ የመመገቢያ ክፍልና የልብስና የመፀዳጃ ዕቃዎች ማስቀመጫና መቀየሪያ ክፍልን ያካተተ ሊሆን ይገባል፡፡
- የክፍሎቹ ውስጣዊ ይዘት እንደሚሰጡት አገልግሎቶች የሚወሰን ሲሆን ከላይ የተገለፁትን ጉዳዮች የሚያሟሉ ሆነው በተጨማሪም የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይገባቸዋል፡፡

**(ሀ) የመኝታ ክፍል:-**

- የመኝታና ማረፊያ ክፍሉ ከህፃናቱ የመጫወቻ ክፍል ጋር ተጎራባች ሆኖ በመጫወቻ ክፍሉ ውስጥ በሚፈጠረው የህፃናት ጩኸት እንዳይረበሽ ድምፅ በማያሳልፍ ቁስ (ማቴሪያል) የተሰራና በከፊል በመስታወት የተከለለ ሊሆን ይገባል፡፡
- የመኝታ ክፍሉ ለተንከባካቢዎች ዕይታ አመቺ ሆኖ በተመሳሳይ ጊዜ የመኝታና የመጫወቻ ክፍሎቹን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
- ክፍሉ በቂ የተፈጥሮ ብርሃን የሚያስገባና በጥላ የተጋረደ ሊሆን የሚገባው ሲሆን ቀጥታ የፀሐይ ጨረር የማያስገባ መሆን አለበት፡፡ በተያያዘም የክፍሉ ሙቀት የተመጣጠነ እንዲሆን ንፁህ አየር ሊዘዋወርበት የሚችልና የተፋፈነ እንዳይሆን ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰው ሰራሽ የሙቀት መቆጣጠሪያ መጠቀም እንዲያስችል ሊደረግ ይገባል፡፡በዚህም መሰረት የመኝታ ክፍሎቹ ይዘት ለጨቅላና ለሚውተረተሩ ህፃናት በተመሳሳይ መልኩ የሚዘጋጁ መሆን ይገባቸዋል፡፡

(ለ) ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመኝታ ክፍሎቹ ከ12 ያልበለጡ ጨቅላ ህፃናትን የሚይዙ ሆነው የክፍሎቹ ስፋት እንደ ህፃናቱ አልጋ የሚለያዩ ይሆናሉ፡፡ ይህም ማለት በክፍሉ ውስጥ የህፃናቱ አልጋ ስፋት ከ75ሳ.ሜ በ 135ሳ.ሜ ያልበለጠ፣ የተንከባካቢዎች የመተላለፊያ ቦታ ከ90 ሳ.ሜ ያላነሰ እና በአልጋዎቹ መካከል የሚኖረው ስፋት ከ45 ሳ.ሜ ያላነሰ ሊሆን ይገባቸዋል፡፡

**(ሐ) የመጫወቻ ክፍል፡-**

- በአጠቃላይክፍሉ ለህፃናቱ በቂ የመዘዋወሪያ ቦታ እንዲኖረው ተደርጎ አቀማመጡም በቂ የተፈጥሮ ብርሃን የሚያስገባና በጥላ የተጋረደ እና ቀጥታ የፀሐይ ጨረር የማያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡

- የክፍሉ ሙቀት የተመጣጠነ እንዲሆን ንፁህ አየር ሊዘዋወርበት የሚችልና የተፋፈነ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ሰው ሰራሽ የሙቀት መቆጣጠሪያ መጠቀም ይቻላል፡፡የመጫወቻ ክፍሉ ወለል ለስላሳና በግጭት ወቅት ጉዳት ሊያስከትል የማይችል ሊሆን ይገባል፡፡
- አዋቂዎች ወደ ህፃናት መጫወቻ ክፍል ከመግባታቸው በፊት ንፅህናቸውን ስለመጠበቃቸውና ህፃናቱን ለበሽታ ከሚዳርጉ ነገሮች ስለመፅዳታቸው ማስጠንቀቂያና ጥቆማ የሚሰጥ ምልክት ከክፍሎቹ በተወሰነ ሜትር ርቀት ላይ በግልፅ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

**(መ) ለጨቅላ ህፃናት (Infant Stage):**

- ለእነዚህ የዕድሜ ደረጃ ህፃናት የሚዘጋጁ የመጫወቻ ክፍሎች ደህንነታቸውና ምቾታቸው የተጠበቀ ሆነው መዘጋጀትና ክፍሎቹም ሞቃትና ለህፃናቱ ዕይታን የሚስቡ ሆነው ሊዘጋጁ ይገባቸዋል፡፡
- አሻንጉሊቶችና ልዩ ልዩ የመጫወቻ ቁሳቁሶች ለህፃናቱ ግልፅና ምቹ የሆነ ክፍት ቦታ ላይ ማስቀመጥና የክፍሉ ግድግዳዎች የሀገርን ባህላዊ እሴቶች የሚያሳዩ ሆነው ሊዘጋጁ ይገባቸዋል፡፡
- በክፍሉ ውስጥ የሚዘጋጁ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና ሼልፎች የማይንቀሳቀሱና ከወለሉ ወይም ከግድግዳው ጋር የተያያዙ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ይህም ህፃናቱ በመዳህ ተነስተው ለመቆም በሚያደርጓቸው ጥረቶች በአካባቢያቸው ያሉትን ወንበር፣ ጠረጴዛና ሼልፎች በመደገፍ ሲሆን በሚደገፉበት ወቅት በመንሸራተት እንዳይከዷቸው ለማድረግ እና አጋዥ እንዲሆኗቸው በማሰብ ነው፡፡
- በዚህም መሰረት አንድ የመጫወቻ ክፍል ከ12 ያልበለጡ ጨቅላ ህፃናትን ለማስተናገድ እንዲቻል እና ለአንድ ህፃን ነፃ የመጫወቻና የመንቀሳቀሻ ቦታ 2.8 ሜ$^2$ ታሳቢ በማድረግ መዘጋጀት ይገባዋል፡፡

**(ሠ) <u>የሚውተረተሩ ህፃናት(Toddler Stage):</u>**ለእነዚህ ህፃናት የሚዘጋጁ የመጫወቻ ክፍሎች

- ለህፃናቱ ነፃነትን የሚሰጡና የሚያበረቷቷቸው ሆነው ሊዘጋጁ ይገባቸዋል፡፡ በዚሁ መሰረት
    - ህጻናት በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ጡንቻዎቻቸው እንዲጠነክሩና እንዲበረቱ እገዛ የሚያደርጉ፣
    - ለእነዚህ ህፃናት የሚቀርቡት የመጫወቻ ቁሳቁሶችና አሻንጉሊቶች የህፃናቱን ዕውቀትና የአዕምሮ ደረጃ ሊያዳብሩ የሚችሉ ሆነው በቀላሉ ሊያገኟቸው በሚችሉባቸውና ቅርብና ግልፅ በሆኑ ቦታዎች ሊቀመጡ ይገባል፡፡
    - ህፃናቱ የሚፈልጓቸውን ቦታዎችና እቃዎች ለመነካካትና ለመለማመድ እንዲሁም አካባቢያቸውን ለማወቅ የሚጠመዱበትና ዕረፍት አልባ የሚሆኑበት የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን ለመጫወቻ የሚዘጋጅላቸው ቦታ ሰፊና ገላጣ ሊሆን ይገባል፡፡
    - የክፍሉ ግድግዳዎች በመማሪያ ፊደላት በእንስሳትና በተክል ስዕሎች የተሞላና የህፃናቱን ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ፣ የማወቅና የመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሳና ዕውቀት የሚያስጨብጣቸው መሆን ይገባዋል፡፡
    - በክፍሉ ውስጥ ህፃናቱን በቡድን ሆነው እንዲጫወቱ መደረጉ ባሉበት ደረጃ ማህበራዊ መስተጋብርን እንዲለማመዱና ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ዕድሉን የሚፈጥሩ መሆን ይገባቸዋል፣

- በዚህም መሰረት አንድ የመጫወቻ ክፍል ከ15 ያልበለጡ የሚውተረተሩ ህፃናትን ለማስተናገድ እንዲቻል እና ለአንድ ህፃን ነፃ የመጫወቻና የመንቀሳቀሻ ቦታ 2.8 ሜ$^2$ ታሳቢ በማድረግ መዘጋጀት ይገባዋል፡፡

**5.3 *የንፅህና መጠበቂያ* ክፍል:-**ይህ ክፍል ለህፃናቱ መፀዳጃና መታጠቢያ የሚያገለግል ሲሆን ከተፀዳዱ በኋላ ልብሳቸውን የሚቀይሩበትና የመፀዳጃ ቁሳቁሶችና አልባሳቶቻቸው የሚቀመጡበት ክፍል ነው፡፡ ክፍሉም በቂ አየር የሚዘዋወርበት ሆኖ ከቀጥታ የፀሐይ ጨረርና ንፋስ የተጠበቀ ሊሆን ይገባዋል፡፡

5.4 ***የምግብ ማዘጋጃና መመገቢያ* ክፍል:-ይህ** ክፍል ጡት የሚጠቡ ህፃናት እናቶቻቸው ለማጥባት በሚመጡበት ወቅት አረፍ ብለው ሊያጠቡ የሚችሉበት ቦታና ተጨማሪ ምግብ የሚጠቀሙ ህፃናት ምግባቸው የሚዘጋጅበትና ከተዘጋጀም በኋላ በወላጅ እናቶቻቸው ወይም በተንከባካቢያቸው አማካኝነት ሊመገቡበት የሚያስችላቸው ቦታ ሊኖረው የሚገባ ሆኖ ክፍሉ በቂ የተፈጥሮ ብርሃን የሚገባበት፣ ንፁህ አየር የሚዘዋወርበትና ቀጥታ የፀሐይ ጨረር የማይገባበት ክፍል ሊሆን ይገባል፡፡ የማብሰያ ክፍሉም ከመመገቢያ ክፍሉ ጋር የተያያዘ ሆኖ ህፃናቱ ሊደርሱበት የማይችሉበትና ለብቻው የተከለለ ሊሆን ይገባዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ለማዕከሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

ይህ ክፍል በማዕከሉ ለህፃናት የተዘጋጁት ክፍሎች እንደሚሰጡት አገልግሎቶች ዓይነት ሊኖራቸው የሚገቡ ቁሳቁሶችን የሚያመላክት ሲሆን የሚቀርቡት ቁሳቁሶች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ እንደተቋሙ ስፋትና እንደሚያስተናግደው ህጻናት ብዛት የሚወሰን ሆኖ በመሰረታዊነት አንድ የህጻናት ማቆያ ማዕከል ከዚህ በታች የተመለከቱትን ቁሳቁሶችን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

### 6 የመኝታ ክፍል

የመኝታ ክፍል ውስጥ በቂ ቁጥር ያለው የህፃናት አልጋና ፍራሽ፣የተለያዩ ተንጠልጣይ ቅርፃቅርፆች፣ የሙቀት መቆጣጠሪያ መሣሪያ (Heater & Air conditioner) አካቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

### 7 የመጫወቻ ክፍል

የቤት ውስጥ የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁስ፣ አሻንጉሊት፣ የህፃናት ወንበርና ጠረጴዛ፣ የፊደል ገበታ፣ ለህፃናት የተዘጋጁ ባህላዊ ስዕሎችና ቅርፃቅርፆች እና ሌሎች ለህፃናት የሚሆኑ የመጫወቻ ቁሳቁሶች የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 8 የንፅህና መጠበቂያ ክፍል

በዚህ ክፍል ውስጥ የዕቃ መደርደሪያ ሳጥን፣ የልብስ መቀየሪያ ጠረጴዛ፣ የህፃናት ማጠቢያ ገንዳ፣ የኤሌክትሪክ ውሃ ማሞቂያ፣ የህፃናት መፀዳጃ ፖፖ፣ የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ሳጥን፣ የህፃናት ንፅህና መጠበቂያ ዳይፐር፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት እና ሌሎች የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን የያዘ ሊሆን ይገባዋል፡፡

### 9 የምግብ ማብሰያና መመገቢያ ክፍል

በማብሰያና መመገቢያ ክፍል የምግብ ማብሰያ ምድጃ (የኤሌክትሪክ እና ሲሊንደር)፣ ፍሪጅ፣ የውሃ ማጣሪያና ማሞቂያ፣ የማብሰያና የመመገቢያ ቁሳቁሶችን ማጠቢያ ቦታ (ሲንክ) እና ማስቀመጫ/መደርደሪያ ሳጥን የያዘ መሆን የሚገባው ሆኖ የመመገቢያ ክፍሉ የህፃናት መመገቢያ ጠረጴዛና ወንበር እና የአዋቂ ወንበር የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡ በማዕከሉ የማብሰያና የመመገቢያ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ መደረጉ አስፈላጊነቱ ለተለያዩ ጉዳዮች ወደ መስሪያ ቤቱ የሚመጡ ተገልጋዮችና

ባለጉዳዮች ህፃን ልጆቻቸውን ይዘው በሚመጡበት ወቅት በማዕከሉ ከማረፊያ አገልግሎት በተጨማሪ ለህፃናቱ በቂና ጤናማ ምግብ ለማቅረብ እንዲያስችላቸው እና በአጠቃላይ የተሟላ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ነው፡፡

**10 የማቆያ ማዕከሉ አስተዳደር**

10.1 ማዕከሉ ተጠሪነት በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ላለው ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ይሆናል፡፡

10.2 የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከማዕከሉ ስራዎች ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ሀላፊነት ይኖረዋል፡፡

(ሀ) በዚህ መመሪያ በተመለከተው መስፈርት መሰረት የህጻናት ማቆያ ማዕከሉ እንዲቋቋም የማድረግ፣

(ለ) ለማዕከሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችና የሰው ሃይል እንዲሟላ ከሰው ሃብት፣ከእቅድና በጀት ጋር በመሆን አስፈላጊው በጀት እንዲያዝ ማድረግ፣

(ሐ) የአካባቢ ፀጥታና ንፅህና መጠበቁን የማረጋገጥ፣

(መ) ማዕከሉን በመወከል ለማዕከሉ አስፈላጊ የሆኑ ስምምነቶችን ማከናወንና ኃላፊነቶችን የመቀበል፡፡

## ክፍል አራት

## በማዕከሉ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች

**11 በማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች**

በማዕከሉ ከዚህ በታች ያሉ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ ይኖርበታል

- የመኝታና የማረፊያ ቦታ አቅርቦትና አገልግሎት፣
- የመጫወቻ ቦታ አቅርቦትና አገልግሎት፣
- የምግብ ማሞቂያ ቦታ አቅርቦትና አገልግሎት፣
- የመመገቢያ ቦታ አቅርቦትና አገልግሎት፣
- የንፅህና መጠበቂያና ለህፃናት የመፀዳጃ ቦታ አቅርቦትና አገልግሎት፣
- የእንክብካቤና የቅርብ ክትትል አገልግሎት፣
- የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና አገልግሎት፣
- የመጫወቻ መዝናኛ አገልግሎት

**12 የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት**

ማዕከሉ የሚከተለውን የአሰራር ስርዓትን ተከትሎ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፣

**12.1 አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት** የህፃናት ማቆያ አገልግሎት መስጫ ማዕከሉ ለተገልጋዮች አገልግሎቱን የሚሰጠው በሳምንቱ የስራ ቀናት ከጠዋት የስራ መግቢያ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽት የሥራ መውጫ ሰዓት ድረስ ሆኖ የምሳ ሰዓት ጊዜንም ይጨምራል፡፡ ሆኖም ተጨማሪ የስራ ቀናትና ሰዓታት ያሉባቸው ተቋማት እንደ አስፈላጊነቱ የስራ ቀናትን መሠረት በማድረግ ሊያሻሽሉት ይገባል፡፡ በመሆኑም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ወላጆች ልጆቻቸውን በተቀመጠው የመግቢያና መውጫ ሰዓት ላይ በመገኘት ለማዕከሉ ተንከባካቢዎች ማስረከብና ሰዓቱንም ጠብቆ በመውጫ ሰዓት ላይ ሄዶ መረከብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

(1) **የአሰራር ስርዓት፡-**

- የማዕከሉን አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ወላጆች ልጆቻቸውንና ራሳቸውን በማዕከሉ ማስመዝገብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን የማዕከሉ ተገልጋይና የህፃኑ ወላጅ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በማዕከሉ የተዘጋጀ ልዩ መታወቂያ ካርድ ተዘጋጅቶ በወላጅና በህፃኑ/ኗ ፎቶግራፍ ተደግፎ (ህፃኑ/ኗ ፎቶ የመነሳት ደረጃ ከደረሱ) የሚሰጥ ይሆናል፡፡
- ወላጆችም ልጆቻቸውን ለማስረከብ በሚመጡበት ወቅት የመታወቂያ ካርድ ይዘው በመቅረብ ካስረከቡ በኋላ ለመረከብ በሚመጡበት ወቅትም ይህንኑ መታወቂያ ካርድ ይዘውና ልጆቻቸውን ተረክበው ስለመረከባቸውም አረጋግጠው ይሄዳሉ፡፡
- ወላጅ መገኘት በማይችሉበት ወቅት ሁለተኛ ወላጅ ማንነትን የሚገልፅ ከህጋዊ የመንግስት አካል የተሰጣቸውን መታወቂያ ካርድ እና ከማዕከሉ የተሰጣቸውን ካርድ አያይዘው በመቅረብ ልጃቸውን መውሰድና ስለመውሰዳቸውም አረጋግጠው ይሄዳሉ፡፡
- የተቋሙ ሠራተኛ ከሆኑት ውጪ የማዕከሉን አገልግሎት ለማግኘት በተቋሙ ለተለያዩ የስብሰባ፣ የስልጠናና መሰል ፕሮግራሞች የሚመጡና ከተቋሙ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ተገልጋዮች የማዕከሉን አገልግሎት ፈልገው በሚመጡበት ወቅት ከመንግስት ህጋዊ አካል የተሰጣቸውን ማንነታቸውን የሚገልፅ የመታወቂያ ካርድ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- እነዚህ ተገልጋዮች አገልግሎቱን በጊዜያዊነት ፈልገው የመጡ ቢሆኑም ልጆቻቸውን በማዕከሉ ለማቆየት ይዘው በሚመጡበት ወቅት በመታወቂያ ካርዳቸው አማካኝነት ምዝገባ ተከናውኖና ለልጃቸው የተሰጠውን ልዩ መለያ (ኮድ)ይዘው መሄድ እንዲችሉና ለመረከብም በሚመጡበት ወቅት በምዝገባ ወቅት የተሰበሰበው መረጃና የመታወቂያ ካርዳቸውን በማመሳከር እንዲሁም ለልጃቸው የተሰጠውን ልዩ መለያ (ኮድ) በማመሳከር ልጃቸውን መረከብና ስለመረከባቸውም ማረጋገጫ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
- በተጨማሪም ለህጻኑ/ኗ የሚያስፈልጉ በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን አልባሳትና ምግቦችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 13 በተጠቃሚዎች ሊሟሉ የሚገባቸው/ግዴታዎች

የማዕከሉ ተገልጋይ የሆኑት ሰራተኞች ከዚህ የሚከተለውን ሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅባለቸዋል፣

13.1 በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ጉዳዮችና መ/ቤቱ አገልግሎቱን የበለጠ ለማጠናከር የሚዘረጋቸውን አሰራሮች የማክበር ፣

13.2 የማዕከሉ የስራ ሰዓት መሰረት ባደረገ ህፃናትን ይዘው በመምጣት ለተንከባካቢዎች የማስረከብና በስራ መውጫ ሰዓት ላይ ሰዓት አክብሮ ህጻኑን/ህጻኗንየመረከብ፣

13.3 ለዕለቱ የሚስፈልገውን በቂ፣ የተመጣጠነ፣ ጤናማና የአስተሻሸግ ስርዓቱን በጠበቀ መልኩ የታሸገ/የተያዘ ምግብ ከመመገቢያ ቁሳቁስ ጋር ለተንከባካቢዎች ተዘጋጅቶ ለህፃኑ የሚቀርብ ከሆነ ከበቂ የምግብ ዓይነቶች ዝርዝርና የአዘገጃጀት ማብራሪያ ፅሁፍ ጋር ተያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.4 አልባሳትን በተመለከተ ለዕለቱ የአየር ሁኔታ የሚስማማና ለዕለቱ የሚሆን በቂ ንፁህ ቅያሪ ልብስ፣ ጫማና ካልሲ፣አንሶላና ብርድልብስ እንዲሁም የቆሸሹና የተቀየሩ ልብሶችን መያዣ የሚሆን ቦርሳ/ከረጢት ጭምር ይዘው መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡

13.5 ወላጅ ልጁን ይዞ ሲመጣ ንፁህ እንዲሆን አጥቦና ንፁህ ልብስ አልብሶ እንዲሁም አቅሙ በፈቀደ መጠን ለህጻኑ/ኗ በማዕከሉ የቆይታ ጊዜው የሚያገለግል በቂ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አዘጋጅቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.6 ወደ ማዕከሉ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ወላጆችና ህፃናት ለተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም ህጻናቱ ከተላላፊ በሽታዎች ነፃ ሲሆኑ ብቻ አገልግሎቱን የሚያገኙ ይሆናሉ፡፡

13.7 ማንኛውም አገልግሎት ፈላጊ ወላጅ ወደ ማዕከሉ አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ ህጻናቱ በዕድሜያቸው የሚሰጠውን ክትባትና የጉበት በሽታ መከላከያ ክትባት መውሰዳቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ፡፡

**14 <u>የሰው ኃይል</u>**

14.1 አገልግሎት መስጫ ማዕከሉእንደሚያስተናግደው ህጻናት ብዛትና የተቋሙ ስፋት አንጻር የሰው ሀይሉ ቁጥር የሚወሰን ሆኖ የተሟላ አገልግሎት መስጠት እንዲያስችለው በበቂ የሰው ኃይል መደራጀት ይኖርበታል፡፡

14.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማዕከሉ ከዚህ በታች የተመለከቱት የሰው ሃይል አሟልቶ መያዝ ይኖርበታለ፡፡

**(ሀ) የህጻናት ተንከባካቢ**

- በህፃናት አያያዝና እንክብካቤ ሙያ ስልጠና ያጠናቀቀች ሆና በመጀመሪያ ዕርዳታ አስፈላጊውን ስልጠና የወሰደች እና በባህሪዋ፣ በፀባይዋና በሥራዋ ምስጉን የሆነች ሴት ተንከባካቢ፤
- አንድ ሞግዚት እስከ6 ህጻናት መንከባከብ ትችላለች ፡፡

**(ለ) የጽዳት ሰራተኛ**

በማዕከሉ የሚገለገሉት ህፃናት እንደመሆናቸው መጠን ህፃናቱ በሚያደርጓቸው የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ችግር እንዳይገጥማቸው የማዕከሉን ፅዳት እየተከታተለችና ከተንከባካቢዎች የሚሰጧትን ጥቆማዎች ባለመሰልቸት ተቀብላ ለመተግበር ፈቃደኛ የሆነች፣በባህሪዋ፣ በፀባይዋና በሥራዋ ምስጉን የሆነች ሴት ጽዳት ሰራተኛ፣ሊኖረው ይገባል፡፡

(ሐ)የመስሪያ ቤቱ የስራ አካባቢና ደህንነት ባለሙያ በተጨማሪ የህጻናቱ ደህንነት ስለመጠበቁ ክትትል በማድረግ ሪፖርት የማቅረብ ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡

**(መ)**ህጻናትን ለመንከባከብ የሚመደቡ ሰራተኞች ከተላላፊ በሽታዎች ነጻ መሆናቸው በሃኪም ማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

**(ሠ)**ህጻናትን ለመከባከብ የተቀጠሩ ሰራተኞች ሆን ብለው ወይም በቸልተኝነት በህጻኑ ላይ ጉዳት ሲያደርሱ በወንጀልና በፍትሃ ብሔር ያለባቸው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት እንዲከሰሱ መደረግ ይኖርበታል፡፡

**15 በጀት**

የማዕከሉ በዚህ መመሪያ ለተገልጋዮች የሚሰጠው አገልግሎትና የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማሟያና ሌሎች ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ወጪ በመንግስት ማስመደብ ይኖርበታል፡፡

## 16 የውጪ የመዝናኛ/መጫወቻ ቦታ

- በአግባቡ የተለየና የታጠረ አካባቢ
- ለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች/ብስክሌት መንሻና ኳስ መጫወቻ ንፁህና የተስተካከለ ቦታ
- ጥሩ እፅዋት ሽፋን፣ የሳር ሜዳና የአበባ ስፍራ ያለው
- በህጻናት ላይ የጤና ጉዳት ከሚያስከትሉ ሁኔታዎች የተጠበቀ ስፍራ

## 17 የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት

17.1 የህጻናት ማቆያ ማዕከል አገልግሎት ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥብቅ ክትትል የሚጠይቅ አገልግሎት በመሆኑ የመ/ቤቱ የስራ አካባቢና ደህንነት ባለሙያ በሳምንት አንድ ቀን በማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት፣ ጊዜውን ጠብቀው አገልግሎቱን እያገኙ ስለመሆኑ፣ የአካባቢውን እና የህጻናትን ንጽህና በአግባቡ መጠበቁን፣ በህጻናት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣ የህጻናት ጤናና ሌሎች በማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ጥብቅና ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥርበማድረግ ሪፖርት ማቅረብ ይኖበታል፡፡

17.2 በተጨማሪም የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በየጊዜው የማዕከሉን ይዘት፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የቁሳቁስ አቅርቦት፣ የአካባቢውን ደህንነትና ሰላም የመገምገም፣ የመከታተልና የመደገፍ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በአካል በማዕከሉ በመሄድ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 18 የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነት

### 1. በህፃናት እንክብካቤ የሞግዚቶች/የሰራተኞች ዝርዝር ሚናና ኃላፊነት

- በአገልግሎቱ የሚሰሩ ሰራተኞች በየጊዜው የተላላፊ በሽታዎች የጤና ምርመራ ማድረግ አለባቸው።
- ከመጮህ፣ መማታት፣ ምግብና መጠጥ ለመስጠት ችላ ማለት፣ በህፃኑ ላይ የስነ ልቦና ወይም አካላዊ ጉዳት ወይም ጥቃት የሚያደርስ ማንኛውንም ባህርይ ከማሳየት መቆጠብ ።
- ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ህፃናት የተመዘገቡና መታወቂያ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።
- ሞግዚቷ ሆን ብላ ህፃን ልጅ የምትጎዳ ከሆነ ይህ በሀገሪቱ ወንጀል ህግ መሠረት አግባብ ባለው ህግ አስከባሪ አካል ምርመራ ተደርጎበት በሞግዚቷ ላይ ከፍተኛ የዲስፐሊን ቅጣት ሊጣልባት ይችላል።
- የክትትልና የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው ማቅረብ።
- አካላዊ ደህንነት፡- ህፃናት እንዳይወድቁ፣ እንዳይጣሉ፣ እንዳይሙቱ ወይም በእንስሳት (በጉንዳን፣በውሻ እና በእባብ) ጥቃት እንዳይደርስባቸው መከላከል።
- ስሜታዊ ደህንነት፡- ህፃናት በክብር እና በፍቅር እንዲያዙ ማድረግ።
- ህፃናት ውጪ በሚጫወቱበት ጊዜ የአየር ጸባዩን ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ እንክብካቤና እዳይቆሽሹ ጥበቃ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

- ለእያንዳንዱ ህፃን የሚከተለውን ዝርዝር መረጃ የያዘ የግል ማህደር ይያዛል፡- የጤና፣የስርዓተ ምግብ፣ የዓካላዊ እድገት፣ የትምህርት እድገት፣ የስሜታዊና መንፈሳዊ እድገት፣ እና የማህበራዊ እድገት።ማንኛውም የግል መረጃ በሚስጥር መያዝ ይኖርበታል።
- በየቀኑ የኪችን፣የመኝታና የመጫወቻ ቦታዎችን ሃይጂን ይጠብቃሉ።
- በተጨማሪም ጠቅላላ የፅዳት ፕሮግራሙን አፈፃፀም ይከታተላሉ ይመዘግባሉ።

## 2. የፅዳት ሰራተኛ

- የማዕከሉን ንጽህና በተመደበው የስራ ሰዓት ህፃናት ከመግባታቸው በፊት ጽዳቱን ማከናወን
- ከንጽህና እና ከጽዳት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች በቂ ትኩረት ማደረግ ።
- ትዕዛዝ እና ግብረመልስ መቀበልና ለህፃናት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ንፁህ ከባቢ ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ።

**3. ወላጅ ወይም የህፃናት እንክብካቤ ተጠቃሚ ዝርዝር ኃላፊነት**

- አንድ ህፃን ወደ ማዕከሉ ከመግባቱ በፊት ወላጆችም ህፃናቱም ከማንኛውም ዓይነት ተላላፊ በሽታ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- የሄፓታይተስ ክትባት ሪኮርድ የሚያሳይ የህፃኑን የክትባት የምስክር ወረቀት ማቅረብ።
- የህፃናት እንክብካቤ አገልግሎትን በሚመለከት በተቋሙ የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችንማክበር።
- ምግብ ጨምሮ ለህፃኑ የሚያስፈልግ ማንኛውም እቃ በአስተማማኝ መያዣ መያዙን ማረጋገጥ።የመመገቢያ እቃዎች (ማንኪያ/ሹካ) ለሞግዚት ይሰጣሉ።
- ምግብ ሙብሰል ወይም በእንክብካቤ አገልግሎቱ መዘጋጀት ካለበት ይህንኑ በአግባቡ ለሞግዚት ማሳወቅ (ለምሳሌ ፈጣን ገንፎ)።
- በአገልግሎቶችና በአገልግሎት ሰጪዎች መተማመን።
- የታመሙ ወይም የደከሙ ህፃናትን አለማምጣት።
- የህፃን ልጅዎን እድገትና ለውጥ መከታተል።
- የህፃን ሞግዚት ግንኙነት ለህፃኑ መልካም አስተዳደግ ተስማሚ መሆኑን በማረጋገጥ ክትትል ማድረግና በአገልግሎት ማሻሻያ እንቅስቃሴዎች በንቃት መሳተፍ።

**4. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት**

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትም በተቋሙ አገልግሎቶች ተቀባይነት አላቸው፣ ሆኖም ማንኛውም አስፈላጊ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

5. **ሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት**

  - ከወላጅ ባህርይ፣ጉዳዮችና ከማህበረሰብ ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች በመፍታት፤አጠቃላይ ትግበራ ይከታተላል።
  - የሕፃናት ማቆያውን ይከታተላል፤
  - የተዘጋጀውን መመሪያና ደንብ ያስፀድቃል፤

**የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ህፃን ወላጅ እናትነትን የሚያሳይ ደብዳቤ ማስፀደቅ።**

1. የህፃኑንና የወላጅ ምስል የያዘ የመታወቂያ ካርድ ማቅረብ።

2 ወላጆች ህፃናት በየእለቱ ቼክሊስት መመዝገባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

3. በመረከቢያ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን በመረከባቸው ማረጋገጫ ይፈርማሉ።

4. በመታወቂያው የተመዘገበ ወላጅ ካልተገኘ ተቋሙ የህፃን አገልግሎት የሚያገኝበት ምትክ

የቤተሰብ አባል ማስፀደቅ አለበት።

5. እናቶች ለልጆቻቸው አስፈላጊ ቁሳቁስ (የምግብና የሳኒቴሽን እቃዎች)፣ የክትባት

የምስክር ወረቀት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

**6. ሌሎች አገልግሎቶችና ሁኔታዎች**

- ✓ **ወላጆች ማምጣት ያለባቸው እቃዎች ዝርዝር፤የሚያስፈልጉ እቃዎች**

  **1 የእጅ ሳሙና**

  **2 ፎጣ**

  **3 አንሶላ/ትራስ ልብስ፣ብርድልብስ**

  **4 ሶፍት**

  **5. (የልጋግ ጨርቅ/ናብኪን/፣ ወተት፣**

  **ምግብ...)፣ዳይፐር የቅያሬ ልብስ**

- ✓ **የህፃናቱ ውሎ ፎርማት**

| ተ.ቁ | የህፃኑ ስም | የደረሰበት | ከቤት የመጡ | በቀን ውስጥ የህፃኑ ሁኔታ | |
|---|---|---|---|---|---|

| | | ሰዓት | እቃዎች | | | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ደስተኛ | አልቃሻ | ተጫዋች | እንቅልፋም | የም/ፍ/ያለው | የም/ፍ/ያጣ | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

**<u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከ --------ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡